ሐምሌ ፲፪ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም. በዓለ ቅዱስ ሚካኤል (19.07. 2012) በፍራንክፈርት ከተማ ለሰላማዊ ሰልፍ በወጡ በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማንያንና ካህናት የቀረበ አቤቱታና ተማኅጽኖ

ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ቆንስላ ጀኔራል ጽ/ቤት
ፍራንክፈርት
<u>ፌዴራል ሪፑብሊክ ጀርመን</u>

## *በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን*

**2**ኛ ግልጽ ደብዳቤ

ጉዳዩ፤ <u>በዋልድባ ገዳምና አካባቢ በልማት ስም የሚደረገዉን እንቅስቃሴና የሚፈርሱትን አብያተ ክርስቲያናት ይመለከታል።</u>

ባለፈዉ **መጋቢት** ወር በዋልድባ ገዳምና አካባቢ በስኳር ልማት ስም የተጀመረዉን እንቅስቃሴ አስመልክተን በዚህ

ስፍራ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት፣ የ**አባቶች** መነኮሳትና **የእናቶች** መነኮ**ሳያ**ት መንፈሳዊ ሕይወት ያንዣበበት አደጋ እንደሚያሰጋን ገልጸናል። በወቅቱም **ለ** ቤተ ክርስቲያናችን የበላይ አካል **ለመንበረ ፓትርያክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት** ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጠን፤ ስጋታችንንም ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲጋራንና ለቅዱሱና ታሪካዊዉ ገዳም ዳር**ደ**ንበር መከበር የበኩሉን እንዲያደርግ ጠይቀን ነበር። ሆኖም እስከ እዚህ ጊዜ ድረስ አንዳችም የተሰጠን ምላሽ በጽ**ሑ**ፍ**ም** ይሁን በቃል አለመኖሩ እጅግ አሳዝኖናል። የቤተ **ክርስቲ**ያንን **ከፍተኛ** ኃላፊነት የተሸከሙ አባቶቻችን የገጠማቸዉ **እክ**ል ባይገለጽልንም አሁንም ድምፃችንን ለሚመለከተዉ ሁሉ ከማሰማት እንዳንቦዝን የእናት ቤተ ክር**ስቲ**ያን ልጅነታችን**ና ሰብኣዊ** **መብታችን** ግድ ብሎናል።

**የተከበራችሁ ወገኖቻችን፤** በተለያዩ መንገዶች ለመረዳት **እንደ**ቻልነዉ አሁንም የተከበረዉን የታሪ**ክ**ና የሃይማኖት **ብሎም ለሽህ ዘመናት የምንኩስና ማዕከል ሁኖ የኖረውን** የዋልድባ ገዳምን ህልዉና የሚፈታተኑ ተግባራት መቀጠላቸዉን፤ የገዳሙ ሃብትና ንብረት መመዝበሩን፤ የግድብ ግንባታዉ ተግባርም ቀን በፀሐይ ብርሃን ሌሊት ደግሞ በመብራት **መቀ**ጠሉን ነዉ። ቀድሞ በዮዲት ጉዲት እና በግራኝ **መ ሐመ**ድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የደረሰባት ፈተናና ያሳለፈችዉ ግፍ አይረሳም። ዛሬ በ**21**ኛዉ **መቶ** ክፍለ ዘመንም ተጨማሪ አበሳ ተፈርዶባት ማየታችን ግን አንድም ያለመታደል፣ **ወይም** ግዴለሽነት ያስከተለዉ መስሎን ሰግተናል። ናቡከደነፆር የቤተ መቅደሱን ንዋየ ቅድሳት ለግል ግብዣዉ መጠቀሙ ያስከተለዉ በጌታ እጅ የተ**ጻ**ፈዉን ወቀሳና ርግማን እንደነበር ስናስታዉ**ስ**፤ **ማንም** በእሳት ይጫወታል ብለን አናስብም። **የንጉሡ የአካብንና የሚስቱ የኤልዛቤልን፣ የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴንና የቴስብያዊውን የኤልያስን ታሪክ መመልከቱ ከታሪክ ተወቃሽነት ያድናል። ያውም ሰሚ ከተገኘ።**

**ካልታጣ ቦታ** የእምነት ቦታን መድፈር፤ ቅዱስና ሃይማኖታዊ ብሎም ታሪካዊ ቅርሶችንም ማጥፋት፤ በማንነት ላይ መቀለድ ካልሆነ በቀር፤ ጨዋነትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዋልድባ ገዳም፤ ያዉም የአባቶ**ቹ** እና **የ** እናቶ**ቹ** አፅም እየፈለሰ፣ **ቤተ ክርስቲያን ጉልላቱ ወርዶ፣ ቤተ መቅደሱና ቅድስተ ቅዱሳኑ ፈርሶ፣ መንበር ከነታቦቱ ተነሥቶ፣ ሥዕልና ንዋየ ቅድሳት ተወግዶ፣ ዐፀደ ቤተ ክርስቲያን ተመንጥሮ** (**ወዘተ**) በለማ የሸንኮራ ተክል ስኳር ተጠቅሞ ይከብራል፤ ጤናም ያገኛል ብለን አናምንም። << **ሰው በዳቦ ብቻ አይኖርምና።**<<

በሌላዉ ዓለም በአንድ ወቅት በሃይማኖት መስመር የተጓዘዉ ቀደምት ትዉልድ የገነባቸዉ አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ ወና ቀርተዉም እንኳን **ሊፍርሱ ይቅርና**፣ ለማደሱም የሚደረግላቸዉን ጥንቃቄ ስናስተዉል፣ **በእኛ ዘንድ ግን** በሺዎች

የሚቆጠሩ መነኮሳት በሃይማኖታዊ ተጋድሎ የተጸመዱበት፤ በተለይም የአክሱሙ ተወላጅ፤ የደብረ በንኮሉ መነኩሴ፤ የበርሃው አንበሳ ሳሙኤል ዘዋልድባ እንደገና ባጠናከሩት፤ መናንያን አባቶችና መናንያት እናቶች ጤዛ ልሰው፤ ድንጋይ ተንተርሰው፤ ጸብአ አጋንንቱን፤ ግርማ ሌሊቱን ታግ ሠው፤ የላመ የጣመ ከመቅመስ ርቀው ቋርፍ (የእንጨት ቅርፊት) እየበሉ <<ኦ እግዚኦ እቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ<< እያሉ ቀንና ሌሊት በተጋደሉበትና በጸለዩበት፤ እንባቸውን እንደ ውኃ ማዕበል በአፈሰሱበት፤ ሁላችን << አስቡን አትርሱን<< እያልን በምንማጸንበት ስፍራ ላይ ( ደወል ደውሎ በመማጸን ለምሳሌ በሩቁ በአፄ ሱስንዮሰ ዘመነ መንግሥት እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ዘቋራጣ ከነተከታዮችዋ፤ በቅርብ ሩቁ በዘመነ መሳፍንት (በአፄ ቴዎድሮስ) ራስ ዓሊ) ሊደረግ የታቀደዉ እጅግ አስገርሞናል። ከዚህም ሌላ እኛ በእጃችን እያለ ያላከበርነዉን የሃይማኖት እና የ ታሪክ ስፍራ ባዕድ እንዴት ያየዉ ይሆን? ማለትም በተገባ ነበር። ለአምስት መቶ ዓመታት በቱርክ ኦቶማን መንግሥት እጅ ወድቆ የነበረው የግሪኩ አቶሰ ገዳም ሳይደፈር በዘመናችን የዋልድባ ገዳም በልማት ስም ሲደፈር ማየትን ኅሊናችን ፈጽሞ ሊቀበለው አልቻለም። እሪ በይ ቤተ ክርሰቲያን፤ እሪ በሉ ገዳማትና አድባራት የሚያሰኘው አሁን ነው።

ስለዘህም በጀርመን አገር የምንገኝ የ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን በደብዳቤ ከወራት በፊት ለጠየቅነዉ ምላሽ በማጣታችን ዳግም በሰልፍ ወጥተን በምንኖርበት ሀገር ድምፃችንን ለማሰማት ተገደናል። በጀርመን ሀገር የሚገኘዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 12ተኛው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ አስተዳደር ለቅዱስ ሚካኤል የሰኔ ክ ብረ በዓል በኮለኝ ካካሄደዉ የሁለት ቀናት ስብሰባ በኋላ ከዚህ እንደሚከተለዉ የሕ ዝበ ክርስቲያኑን ና የካህናቱን አቤቱታዎች በመዘርዘር ዳግም ጉዳዩ ን ለሚመለከታቸዉ አካላት ያቀርባል፤ ለሕዝብ የመገናኛ አውታሮችም እንዲገለጽ ወስኗል።

- *በዋልድባ ታሪካዊ ገዳ ም ላይ በስኳር ልማት ስም የተጀመረዉ ቤተ ክርስቲያንና ታሪክን የሚያፈርስ እንቅስቃሴ ባስቸኳይ እንዲቆም*
- *የተዘረፈዉና የተመዘበረዉ የዋልድባ ገዳም ንብረት ባስቸኳይ እንዲመለስ*
- ***ነፍስ ለገደለ፤ ቋንጃ ለቆረጠ ሁሉ መማጸኛ ሆኖ በኖረ ገዳም ውስጥ የሚገኙ አ ባቶች መነኮሳት ና እናቶች መነኮሳያት ዛሬም በስጋት ላይ መኖራቸዉ ግልጽ ነዉና የሃይማኖት እኩልነት ብሎም ነፃነት አለባት በምትባለዉ ሀገ ራችን መንፈሳዊ ነፃነታቸዉ እንዲከበር***
- ***በዓለም ውስጥ ሲኖሩ ከዓለሙ ተለይተው የሚኖሩ አባቶች መነኮሳትና እናቶች መነኮሳያት ገዳማዊ ሕይወታቸው ብሎም ቅዱሱ ገዳማችን ሳይደፈር ያለምክንያት የደወል ድምፅ አላሰሙምና ጩኸታቸው ጩኸታችን፤ ሰጋታቸው ስጋታችን፤ ኀዘናቸው ኀዘናችን፤ ጭንቀታቸው ጭንቀታችን መሆኑ እንዲታወቅልን***
- *የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች የምዕመናንን ድምፅ በማስተጋባት የዋልድባ ገዳም መነኮሳትን ከተጋረጠባቸዉ ሰዉ ሠራሽ ፈተና ለመታደግ እንዲነሡ*
- *ዋልድባ ገዳምን በአቅማቸዉም ሆነ በእዉቀታቸዉ ለመርዳት ወደስፍራዉ የሚሄዱ ምዕመናን ቀድሞ እንደነበረዉ በነፃነት እንዲሄዱ፤ የተቀመጡ ኬላዎች እንዲነሡ እና እነሱንም ማሸማቀቁ እንዲቆም፤ ያካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ጥያቄም ሰሚ እንዲያገኝ*

- በኃላፊነት ወንበር የተቀመጡ አባቶቻችን በገዳሙ ውስጥና በዙሪያው ያሉ ሚሊሻዎች ከአካባቢው እንዲወጡ ከሚመለከተው አካል ጋር እንዲነጋገሩ

- ሃይማኖት ምድራዊ ትርፍ የሚገኝበት እንዳለሆነ ግልጽ ነዉና ምዕመናንን ለእምነታቸዉ በሚያደርጉት መንፈሳዊ አገልግሎት ማበረታታት የቤተ ክርስቲያንና የ ቤተ ክህነት ዋነኛ ተልዕኮ መሆኑ በተግባር እንዲገለጽ

- ቤተ ክህነት በሃይማኖታዊ ስፍራዎች ላይ የደረሱ ጥቃቶች ተመርምረዉ ጥፋተኞቹ እንዲጠየቁና እንዲታረሙ በሚመለከተዉ አካል ላይ ተገቢዉን ግፊት እንዲያደርግ

- በዋልድባ ገዳም ላይ የሚደረገዉንም ሆነ በሌሎች ገደማት ላይ የደረሱትን ጥቃቶች በይፋ ለምን ተደረጉ ብሎ ሥጋትን መግለጽ የፖለቲካ ፍጀታና ጥያቄ ሳይሆን የእምነትና ለእምነት ነፃነት መከበር መቆም መሆኑ እንዲታወቅልን እንጠይቃለን።

- << መንግሥት ችግር እንደሌለ አድርጎ >> ይናገራል። እንደሚለው ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ገለልተኛ በሆነ አካል ይጣራ ዘንድ እናሳስባለን።

- የሰሜኑ ሀገራችን መሬት ቆዳው ተገፎ፤ ሥጋው ተብልቶ፤ አጥንቱ ገጦ ሲታይ የዋልድባ ገዳም ግን በተፈጥሮ ደን የተሸፈነ በመሆኑ ለትናቷና ለዛሬዋ ኢትዮጵያ ቋሚ የጋራ ቅርሳችን ነውና መንግሥት የከበዱ እጆቹን ከዚያ እንዲነሣ እንማፀናለን።

አሁንም ተገቢዉን ምላሽ እስክናገኝ የቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆነዉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጩኸታችንን እንዲሰማ፤ ኃዘንና ልቅሷችንንም እንዲቀበል ይግባኝ ለክርስቶስ እያልን ጸሎታችንን እንቀጥላለን። **UNESCO** እና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ም/ቤት፤ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አባቶችና ተቋማት፤ ለአካባቢ ተፈጥሮ ጥበቃ የቆሙ አካላትን ጨምሮ ሌሎች ታሪክና ቅርስ እንዲጠበቅ የሚንቀሳቀሱ ዓለም ዓቀፍ ተቋማትም እየደረሰ ያለዉን ጥፋት እንዲያዉቁና ለማስቆም የበኩላቸዉን እገዛ እንዲያደርጉም እናሳስባለን።

ልዑል አምላካችን አፅራረ ቤተ ክርስቲያንን ያስታግስልን፤ የቤተ ክርስቲያናችንንም ት ንሣኤ ያሳየ ን፤ የንጹ ሐን መንፈሳ ውያን አባቶቻችንን እና እናቶቻችንን እንባ እግዚአብሔር ያብስልን!

ቸሩ መድኃኔዓለም እንደ ዔደን ገነት በአራት ወንዞች የተከበበውን፤ ጥንታዊዉን ገዳም ዋልድባንና የአካባቢውን አብያተ ክርስቲያናት በልማት ስም ከመጣ ጥፋት ይሰውርልን።

ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን፤ ቸርነቱም ከሀገራችን ጋር ይሁን!

ስለ ሰላማዊ ሰልፉ ዝግጅት ኃላፊ

ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ

Ueckeratherstr. 2, D- 50739 Koeln, Germany

ከዚህ ቀጥሎ ቅድመ ዝግጅቶችን እንገልጻለን፤

፩ኛ የሥነ ልቡናና የሥነ አእምሮ ዝግጅት ማድረግ

፪ኛ የሰላማዊ ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴ በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑና በየጽዋ ማኅበራቱ እንዲቋቋም ***መመሪያ መስጠት***

፫ኛ ሰላማዊ ሰልፍ የምናደርግ**ባ**በት ቀን ዕለተ ሐሙስ እንደመሆኑ መጠን ከሰኞ እስከ ረቡዕ፤ ከሐምሌ **፱-.፲፩ ፳፻፬ ዓ.ም.** (16.-18.07.2012) ለሦስት ቀን እንደ ነነዌ ሰዎች የጾምና የምኅላ ቀናት እንዲሆኑ ማወጅ፤ ከተቻለ በሀገር ቤትና በውጭ አህጉራት ያሉ መነኮሳትና መነኮስያት፤ ካህናትና ዲያቆናት፤ ምእመናንና ምእመናት በጾም፥በጸሎትና በምኅላ እንዲተባበሩ መንፈሳዊ ጥሪ ማስተላለፍ

፬ኛ ጥላና ድባብ፤ ሥዕለ አድኅኖና ኩራተ ርእስ፣ ቃጭልና የመጾር መስቀል፤ ከተገኘም ጥሩባና ቀንደመለከት ይዞ መውጣት

አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በኃይል የመጣ ግብረ ኃይልን የሚቋቋሙበት ግብረ ኃይል ወይም ክፍለ ጦር የላቸውም። ያላቸው መሣሪያ በተራ ቁጥር ፫ እና ፬ የተገለጹት ናቸውና በተግባር ለማዋል ወደ **ሕያው** እግዚአብሔር ያለማቋረጥ መጮህ ተገቢ ነው፥



0 km 50
TƎGRAY
ᶜAdwa
Ǝnda Śəllase
Aksum
Täkkäze
Waldəbba
ᶜAddi Arqay
Ṣällämt
Wälqayt
ᶜAbiy ᶜAddi
Däbarq
Səmen
Abärgälle
BÄGEMDƎR
Dabat
Wägära
Gondär
Aykäl
Addis Zämän
Ṭana